# 1. በዓለም እየሆነ ያለዉ ምንድን ነው?

## በዚህ ትምህርት የሚያጠኗቸዉ

እውነትን ማወቅ የሚችሉት እንዴት ነው?

ዓለም እንዴት ተጀመረች?

ዓለም የገጠማት ብልሽት ምንድን ነዉ?

ዓለም ምን ተስፋ አላት?

## ክፍል 1

### እውነትን ማወቅ የሚችሉት እንዴት ነው?

**ከሳይንስ፣ ታሪክ እና የህይወት ልምምድ**

ስለዓለም እና በውስጧ ስለሚኖሩ ሕዝቦች ከሳይንስ፣ ከታሪክ፣ እና ከማየት ብዙ ድንቅ ነገሮችን መማር ይችላሉ። ይሁን እንጂ ለአብዛኞቹ አበይት ጥያቄዎች መልሳቸውን ከእነዚህ ምንጮች ማግኘት አይችሉም። ሕይወት እንዴት እንደተጀመረ፣ ዓላማው ምን እንደሆነ እና ወደፊት ምን እንደሚጠብቀዉ አይናገሩም።

**ከ<u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>**

ዓለም ለምን እና እንዴት እንደሰራች በትክክል ሊነግርዎ የሚችል ሰሪው ብቻ ነው። እርሱ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ስለእነዚህ እውነታዎች ይነግረናል። በዚህ ዓለም ለመኖር የሚያስችለንን ትክክለኛ መመሪያ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው።

**ይህ የሕይወት ዓበትይ ጥያቄዎች ኮርስ**

እነዚህ ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ለጥያቄዎችዎ መልስ ከሚሆኑት በርካታ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳሉ። ከእያንዳንዱ ጥቅስ በፊት የሚገኝበት ምዕራፍና ቁጥር ይጠቀሳል። ይህም የመጽሐፍን ስም፣ ምዕራፍ እና ቃሉ የሚገኙበትን ቁጥር የሚያካትት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከተጻፈባቸው ቋንቋዎች ወደተለያዩ ቋንቋዎች ስለተተረጎመ ብዙ ትርጉሞች አሉ። እዚህ ላይ የሚጠቀሱት የእግዚአብሔር ቃሎች እርስዎ ካሉዎት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር ትንሽ የተለዩ ወይም

አንድ አይነት ሊሆኑ ይችላሉ:: እዚህ ላይ የተጠቀሱት ከቀድሞው ትርጉም /1962/ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እና በ1993 ዓ.ም ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው::

# ክፍል 2

## ዓለም እንዴት ተጀመረች?

### እንዲሁ ተገኘች?

ዓለም ከየት መጣች? እንዲሁ ተገኘች ወይስ ታላቅ አዕምሮ ዕቅዷት በታላቅ ኃይሉ ሰራት ብለዉ ራስዎን ጠይቀዉ ያውቃሉ?

መኪና ወይም አውሮፕላን በሚያዩበት ጊዜ እንዲሁ እንዳልተገኙ ያውቃሉ:: በተወሰነ የአሰራር ዘዴ እንዲንቀሳቀሱ አድርጎ ያቀደ እና የሰራቸው ሰው አለ::

### ዓለም የተፈጠረችዉ በዕቅድ ነዉ

ዓለም እና በውስጧ ያሉ ነገሮች በሙሉ እየሰሩ ያሉት በአንድ የተወሰነ ስርዓት ሲሆን ይህንም የተፈጥሮ ህግ ብለን እንጠራዋለን:: ሳይንስ ስለእነዚህ የተፈጥሮ ህጎች ብዙ ግኝት ባደረገ ቁጥር አጠቃላዩን ፍጥረተ ዓለም በዕቅዱ መሰረት ፈጥሮ በስርዓት የሚያስኬድ እና የሚጠብቀው አንድ አካል እንዳለ እናውቃለን:: እርሱም ሁሉን ቻይ እና ሁሉን አዋቂ የሆነው ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው:: እርሱ ጌታ እና የፍጥረት ሁሉ ገዢ ነው::

**እነዚህን ጥቅሶች በቃልዎ ይያዙ**

**ዘፍ1:1** በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ::

**ዮሐ1:3** ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል::

### እግዚአብሔር የፈጠረዉ ፍጹም የሆነችን ዓለም ነዉ::

እግዚአብሔር ጸሐይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን እና መሬትን ፈጠረ:: አንዳቸው ከሌላቸው ጋር እንዳይጋጩ ምህዋር አበጀላቸው:: በመሬት እና በጸሐይ መካከል ያለው ዕርቀት በጣም ተቀራርበው ሁሉም ነገር እንዳይቃጠል ወይም ደግሞ በጣም ተራርቀው ሁሉም ነገር በረዶ እንዳይሆን በትክክለኛ ዕርቀት ላይ አስቀመጣቸው:: ውቅያኖስ እና የብስ ፍጹም የሆነ

ተመጣጣኝነት ያላቸው እና ከባቢ አየሩም ትክክለኛ ነበር:: ከዚያም እግዚአብሔር ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ፈጠረ:: ከሁሉም በመጨረሻ ሰውን ፈጥሮ ውብ እና ድንቅ በሆነች ዓለም ውስጥ አስቀመጠው::

**ይህን ቁጥር በቃልዎ ይያዙ**

**ዘፍ 1:31** እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበር::

## እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረበት ምክንያት

እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረ በፍጥረቱ ደስ ለመሰኘት ነው:: ሰዎችን የፈጠረው ደግሞ ልጆቹ እንዲሆኑ፣ እንዲወዳቸው እና በእነርሱ ደስ እንዲለው ነው:: ምድርን የሰራት ለእነርሱ መኖሪያነት ነው:: እግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለሙን ውበት እና ስርዓት እያየ መደሰት ይችላል ነገር ግን ከሁሉም በላይ የሚያስደስተው ነገር ለልጆቹ ያለው ፍቅር ነው::

**ራዕይ 4:11** አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፣ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና ሆነዋልምና::

**መዝ 149: 4** እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይለዋልና::

እግዚአብሔር ልጆቹ እንደእርሱ እንዲሆኑና ከስራው ተካፋይ እንዲሆኑ ፍላጎቱ ነበር:: ስለሆነም ለመጀመሪያው ወንድ አዳም እና ለመጀመሪያዋ ሴት ሔዋን በብዙ መልኩ ከራሱ ጋር የሚቀራረብ ባህሪ ሰጣቸው:: እግዚአብሔር ያስተምራቸው ነበር:: በእርሱ ዕርዳታ ሰው ምድርን መግዛት ይችል ነበር::

**ዘፍጥረት 1:26** "እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንስራ . . . በምድር ሁሉ ላይ ስልጣን ይኑራቸው::"

**ይህን ይስሩ**

- ዓለም ለምን እና እንዴት እንደተሰራች የሚነግረን መጽሐፍ የቱ ነው?
- የተፈጥሮ ህግ ብለን የምንጠራቸውን የፍጥረተ ዓለም ስርዓቶች የመሰረተው ማን ነው?
- ዓለም የተፈጠረችው ለማን ደስታ ነው?
- ዓለም መጥፎ ነበረች ወይስ መልካም ?

- እግዚአብሔር ለዓዳምና ሔዋን የሰጣቸው ባህሪ እንደማን ነበር?
- የእግዚአብሔር ፍላጎት ሰዎች በፍቅሩ እንዲረኩ እና የእርሱ_________እንዲሆኑ ነበር።
- በ _________ እርዳታ ሰው በ _________ላይ ስልጣን እንዲኖረው ታቅዶለት ነበር።

*ያጠኑትን ክፍል ወደኋላ ተመልሰዉ በማየት መልሶችዎን ያመሳክሩ። በትክክል ያልመለሱት ካለ ያስተካክሉት።*

# ክፍል 3

## ዓለም የገጠማት ብልሽት ምንድን ነዉ?

### አንድ ስህተት ተፈጠረ

ዙሪያዎን ሲመለከቱ መከራን፣ ሐዘንን፣ ጠብን፣ አመጽን፣ ጦርነትን፣ ረሐብን፣ እና ሞትን ያያሉ። ዓለም አሁን ፍጹም አይደለችም። የተፈጸመው ስህተት ምን ነበር? ይህች በአንድ ወቅት ፍጹም የነበረችዋ ዓለም በእግዚአብሔር ጠላት እና በራሱ በሰው ተበከለች።

### የእግዚአብሔር ጠላት

እግዚአብሔር ሰይጣን ወይም ዲያቢሎስ የሚባል ጠላት አለው። በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነበር። ነገር ግን ትዕቢተኛ እና አመጸኛ ሆነ። አሁን ሰይጣት እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ይቃወማል። እግዚአብሔር ሊረዳን ይፈልጋል፣ ሰይጣን ሊያጠፋን ይጥራል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ባለው ፍቅር እና ህብረት ሊደሰት ይፈልጋል። ነገር ግን ዲያቢሎስ ከእግዚአብሔር ሊለየን ይጥራል። ሰይጣን ከእግዚአብሔር ይልቅ ዕርሱን እንድንከተለው ለማድረግ ጥረት ያደርጋል።

## የሰው ሐጢአት

ሰይጣን ለአዳም እና ሔዋን ስለእግዚአብሔር ውሸት ነገራቸው። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዲያደርጉ ማለትም እንዳይታዘዙ አሳመናቸው። ሰውን ከእግዚአብሔር ስለሚለይ ኃጢአት ሞትን እንደሚያመጣ እግዚአብሔር አዳምን አስጠንቅቆት ነበር። ሕይወት የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ከእርሱ መለየት ፍጻሜው ሞት ነው። አዳም እና ሔዋን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰይጣንን ለማመን መረጡ። የእግዚአብሔርን ህግጋት ጥሰው የራሳቸውን መንገድ በመከተል ለዓለም ሁሉ አስከፊ ጥፋትን አመጡ።

## የኃጢአት ውጤቶች

ኃጢአት በዓለም ላይ በሽታን እና ሞትን አስከትሏል።

**ሮሜ 5፡12** «ስለዚህ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደገባ ሁሉ፣ ሞትም በኃጢአት በኩል ገብቶአል። በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፣ ምክንያቱም ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል። »

ኃጢአት በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል የነበረውን ህብረት አበላሸው። ሰው ዓመጸኛ የማይታዘዝ እና ኃጢአተኛ እስከሆነ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ሊኖረው አይችልም። የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑ ቀርቶ የኃጢአት አገልጋይ ይሆናል።

**ሮሜ 6፡16** *ራሳችሁን እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ ለምትታዘዙት ለእርሱ ይኸውም ወደ ሞት ለሚወስደው ለኃጢአት ወይም ወደ ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ ባሮች እንደሆናችሁ አታውቁምን?*

እግዚአብሔርን ባለመታዘዛችን ከሰይጣን ዓመጽ ጋር ተባብረን አገዛዙን መቀበላችን ነው። ምድር እግዚአብሔር እና ሰይጣን የሚዋጉባት የጦር ሜዳ ሆናለች። ከየትኛው ወገን እንደሚሆኑ መምረጥ አለብዎ።

## ***ምርጫዎ የእግዚአብሔር መንገድ ነዉ ወይስ የሰይጣን መንገድ?***

**ኢያሱ 24፡15** *"የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።"*

<u>እግዚአብሔር የሚሰጠን</u>

**በተፈጥሮ ውስጥ**

ፍፁም ፍጥረት ዓለም

የተትረፈረፈ በረከት

ሚዛናዊነትና ስርዓት

**በአካላችን ውስጥ**

ህይወት እና ጤንነት

ጤናማ መሻቶች

**በአስተሳሰባችን፣በስሜታችንእና በድርጊታችን**

ንጹህ ፍቅር በጎ ሐሳቦች የመምረጥ ነጻነት

ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት መታዘዝ፣ ጠቃሚነት፣ ደስተኛነት ከፍርሃት ነጻ መሆን፣

ትህትና፣ ዓላማ እውነት፣ እምነት፣ ፍትህ፣ ሰላም፣ ታማኝነት፣ ጥበብ የፈጠራ ችሎታ፣ ደስታ።

<u>ሰይጣን የሚሰጠን</u>

**በተፈጥሮ ውስጥ**

የተበከለ ተፈጥሮ

ስርዓት አልባነት ድህነት

ቅርፅ ዓልባነት ርሐብ

**በአካላችንውስጥ**

በሽታነ ሞት

ክፋት

የስጋ ምኞት

**በአስተሳሰባችን፣በስሜታችንእና በድርጊታችን**

የኃጢአት ባሪያነት

ከእግዚአብሔር መለየት ዓመጸኛነት ራስ ወዳድነት፣ ወዳድነት፣ ወንጀል፣ ዓላማቢስነት፣ ጦርነት፣ ጥላቻ፣

ክፉ ሐሳብ፣ ጥፋት፣ ሐዘን፣ ዓለማመን፣ ትዕቢት፣ ተጠራጣሪነት፣ ስህተት፣ ኢፍትሐዊነት፣ ፍርሃት፣ ጠብ፣ ውድቀት።

## ይህን ይስሩ

በሰንጠረዡ ውስጥ ከተዘረዘሩት መካከል ከሚፈልጉአቸው ጎን የ(x)ምልክት ያድርጉ በማይፈልጉአቸው ጎን ደግሞ (0)ን ያድርጉ::

ምልክት ባደረገት መሰረት፦ መሁን የሚፈልጉት ከእግዚአብሔር ጎን ነዉ ወይስ ከሰይጣን?-------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

# ክፍል 4

## ዓለም ምን ተስፋ አላት?

### አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ለዓለም ግድ ይለዋል::

ምንም እንኳ ሐጢአተኞች ብንሆን አሁንም እግዚአብሔር ይወደናል:: ከኃጢአት፣ ከሰይጣን፣ እና ከዘላለም ሞት እኛን የሚያወጣበት መንገድ አዘጋጅቷል:: አሁንም ቢሆን ፍጥረተ ዓለምን የሚገዛ እግዚአብሔር ስለሆነ አንድ ቀን ምድርን ሁሉ እንደገና ወደመታዘዝ ያመጣታል::

### የእግዚአብሔር ልጅ የእኛን ቅጣት ተቀበለ

በምድር ላይ ማንኛውም ሰው ኃጢአትን የሰራ እና የሞት ፍርድ የተወሰነበት ነው:: ራሳችንን የምናድንበት ምንም መንገድ አልነበረንም:: እግዚአብሔር እጅግ ስለወደደን የእኛን ቅጣት ይቀበል ዘንድ አንድያ ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ላከው::

የዛሬ 2000 ዓመት አካባቢ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በመምጣት መለኮታዊ በሆነ መንገድ ከአንድ ድንግል ሴት በፍልስጤም ምድር ተወለደ:: የእግዚአብሔርን እውነት እና ፍቅሩን ለሰዎች አስተማረ፣ በህይወቱ ሁሉ ምንም ስህተት አልፈጸመም:: እያንዳንዱን ሰው በአክብሮት እና በርህራሔ ያይ ነበር:: ነገር ግን እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ በመስቀል ላይ ተሰቀለና ሞተ:: ለኃጢአታችን ሲል ሞተ:: እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞተ በሶስተኛው ቀን

በሕይወት በማስነሳት ልጁ መሆኑን ለአለም ሁሉ አሳየ። ከሞት ከተነሳ ከአርባ ቀናት በኋላ ኢየሱስ ተመልሶ ወደ ሰማይ ዐረገ። ከትንሳኤው በኋላ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያዩት የኢየሱስ ወዳጆች በወንጌላት ላይ ስለዚህ ታሪክ ነግረውናል።

## ኢየሱስን መቀበል የእግዚአብሔር ልጆች ያደርገናል።

ዕርሱ ቅጣታችንን ስለተቀበለ አዳኛቸው አድርገው የሚቀበሉት ከኃጢአት ኃይል ነጻ ይወጣሉ። ከኃጢአታችን ስንመለስ እግዚአብሔር ህይወት ይሰጠን እና ልጆቹ ያደርገናል። በልጁ በማመን ከኃጢአት እንድንድን እግዚአብሔር ያሳስበናል፣ ሆኖም ግን አያስገድደንም።

**ሮሜ 5፡17** «በአንድ ሰው መተላለፍ ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሰ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕይወት አይነግሱ።»

| |
|---|
| **የሚከተሉትን ጥቅሶች በማጥናት በቃልዎ ይያዙ** |
| **1ዮሐ 3፡16** «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና።» |
| **ሮሜ 6፡23** «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው»። |

## ፍጹም በሆነች ዓለም ውስጥ መኖር ይችላሉ

ዓለምን ከኃጢአት ሊያነጻ እና ሁሉን ነገር አዲስ ለማድረግ ኢየሱስ አንድ ቀን ተመልሶ ይመጣል። አሁን አዳኝዎ አድርገዉ ከተቀበሉት በዚያን ጊዜ ፍጹም በሆነ ደስታ ውስጥ ከእርሱ ጋር ይኖራሉ። አሁን በሚኖሩት ህይወትም ኢየሱስ በውስጥዎ ለመኖር ስለሚመጣ የተሻለ ህይወት እንዲኖርዎና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር እንዲያደርጉ ያስችልዎታል። ለእግዚአብሔር ልጆች የተዘጋጀውን በረከት ከዛሬ ጀምረዉ ተካፋይ መሆን ይችላሉ።

| |
|---|
| **ይሚከተለዉን ይስሩ** |
| **በክፍት ቦታዎች ላይ ስምዎን ይጻፉ** |
| የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ____________________ እንዲሁ ወዷልና። |

ኢየሱስን አዳኝዎ አድርገዉ አሁን መቀበል ከፈለጉ የሚከተለዉን ጸሎት ይጸልዩ።

# ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ ስለወደድከኝ እና ስለኃጢአቴ ይሞት ዘንድ ልጅህን ስለላከው አመሰግንሃለሁ። አሁን ኢየሱስን አዳኜ አድግጌ እቀበላለሁ። በቀረው የሕይወት ዘመኔ ሁሉ ከሰይጣን ጎን ሳይሆን ከአንተ ጎን መሆን እፈልጋለሁ። እንድሆንልህ የምትፈልገውን አይነት ሰው ታደርገኝ ዘንድ እለምንሃለሁ።በኢየሱስ ስም። አሜን።*

<u>ክፍለ ትምህርት አንድን በማጠናቀቅዎ እንኳን ደስ አለዎ!</u>

በዚህ አጭር የመማሪያ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ወደቀረቡ የትምህርቱ መከለሻ ጥያቄዎች በመሄድ የክፍለ ትምህርቱን ጥያቄዎች ይመልሱ። ከዚያም ወደ ሚቀጥለዉ ትምህርት በመግባት ጥናትዎን ይቀጥሉ።

*እግዚአብሔር ይባርክዎ!*